# ማኅሌት

እራቱ ተበልቶ፣ ማእዱ ተነስቶ
ወሬ ሲያጣጥሙ፣ ኩራዙም በርቶ
ማኅሌት በልጅነት ስታዳምጥ ነቅታ
“ልጄ፣ ይበቃሻል፣ ሂጂ ከመኝታ…”
ብለው ቢሸኟትም፣ የተኛች መስላ
ወሬ ትቀስም ነበር የሚሉትን ሁላ።

ጠላ እየጠጡ፣ ቆሎም እየበሉ
በልጅነታቸው፣ ኋላም ከፍ እንዳሉ
እነ አባባ ያዕቆብ በሽፍትነት ሳሉ
ሽማግሌዎቹ የሆነውን ሁሉ
የድሮው ከዛሬው እየቀላቀሉ
ያወሩ ነበረ እያሰላሰሉ።

ይህን እየሰማች ዕንቅልፍ ሲወስዳት
በሕልሟ እየመጣ ወትሮ የሚታያት
“አድርሺው ልጄ ሆይ ይህንን ቁም-ነገር
ጳውሎስና ጴጥሮስ ከሞቱበት ኣገር…”
ኣባባ ያዕቆብም እጅግ የሚወዱት
ኣደራ ኣስይዘው ሩቅ ኣገር ሲሰዱት

የተቋጠረ ዕቃ ይዛ ስትሄድ
ከማታውቀ አገር ጠፍቶባት መንገድ
“እማየ! ጠፋብኝ” እያለች ነቅታ
ብንን ትላለች ከዕንቅልፏ ተነስታ
ኣይዞሽ ልጄ!” ሲሉ፣ ሲያባብሉ ኣክስቷ
ድንጋጤው ጠፍቶ፣ ያቆማል ጩኸቷ

ማኅሌት በልጅነት እንዲህ እያደገች
የዚህ ሕልም ፍቺ ምን ይሆን እያለች
ቡና ሲቆላና፣ ሙቀጫ ሲወቅጡ
ቁርስ ሲበላና፣ ቡናውም ሲጠጡ
ሌሊት ያለምኩትን ፍቱልኝ እያለች
ሽማግሌዎቹን ትጠይቅ ነበረች

ሽማግሌዎቹም ዛሬስ ሕፃን ነሺ
ትንሽ ከፍ ብልሽ ከልጅነትሺ

እንነግርሻለን ለሞያ ስትደርሺ
ቁም-ነገር ኣለ እንጂ የምትወስጂው
ለሩቅ ኣገር ሰዎች የምትነግሪው

ትንሽ ከፍ እንዳለች ምስጢሩን ሳይነግሯት
ለትምህርት ብለው ውጭ ኣገር ሰደዱት
ዘመናቱ ሄዱ፣ ትምህርቱም ተገፋ
የውጭ ኣገር ኑሮ፣ ስንቱን አሳልፋ
ነገሩን ረሳችው፣ ሕልሞቹም ኣበቁ
ሽማግሌዎቹም እየሞቱ ኣለቁ

ማኅሌት ተመልሳ ከኣገሯ ስትመጣ
ከቤተሰቦቿም ግማሹን ልታጣ
መጣች ተመልሳ አይታ በዙ ዓለም
ያአገሯ ናፍቆት ጠንቶባት በጣም
እክስቷ እማሆይ እኛ መነኰሲት
ኣባባ ያዕቆብም ሞተው ቆይዋት

ተላቅሰው፣ ኣልቅሰው ሁሉም ተቀበሏት
ትንሽ ሰንበት ብሎም ናፍቆት ሳይወጣላት
የሰንቤቴ ጸበል ጐረቤት ተጠርታ
ጸዲቅ-ጸበሉንም ተሳልማ፣ ጠጥታ
ኣንድ ኣዝማሪ ኣየች ዓይኑ የታወረ
ብዙ ድንቅ ነገርም ያወራ ነበረ

አሮን የተባለ የሰፈሩ አዝማሪ
መሰንቆና፣ ክራር፣ በገናም ደርዳሪ
በየጠበሉና፣ በሓዘንም ቤት፣
በየሰርጉም ቦታ ሄዶ ሲጫወት
ታሪክ ኣያይዞ ብዙ ሲናገር
አድማጩን ሰው ሁሉ ያስለቅስ ነበር

ቋንቋውን ዘንግታው ሲተረጉሙላት
ድሮ የረሳችውን ሕልሟን ከሰቱላት
ኣሮን ኣዝማሪው ዛሬ ታውሯል
በልጅነቱማ ለካ ኣርበኛ ኖሯል
ከኣባ ያዕቆብና ከማሆይ ወለቱ
ስንት ጀብዱ ሠሩ በአንድነት ሦስቱ

“እግዜር ዕድሜ ሰጥቶን ደግ መቆየት
ጠፍተሽ ቀረሽ ብለን ብዙ ከመስጋት
እንኳን ደህና መጣሽ የኛይቱ ማኅሌት!

“ስሚኝ ልነግርሽ ነው ድሮ የሆነውን
በወረራ ዘመን የተፈጸመውን
ወደ ሮማ ወስደሽ የምትነግሪውን

“ሶላቶች ነበሩ በጥጋብ ያበዱ
ኣገራችን ወርረው እጅግ የቀለዱ
የሠሩት’ማ ግፍ ብዙ ነዋ ጉዱ

“ስንቱን በግፍ ፈጁት፣ ጭቆናው ከረረ
ከሞት የተረፈው እየተማረረ
ወደ ሽፍትነቱ ገባ እየበረረ

“ብዙ ሰው ያን ጊዜ ከዱር ሲሰማራ
ኣክስትሽ ዓለም-ጣይ ከያዕቆብ ጋራ
ኣብረን ተጉዘናል ጋራና ተራራ

“ተከዜ ከኣፋፉ እነ ራስ እምሩ
ከነ ጭፍሮቻቸው ፊታውራሪም ብሩ
ኣረ ስንቱ ጀግና፣ ሌሎችም ነበሩ

“ያ ቆራጡ ጀግና ባላምባራስ ተሰማ
ሶላቶውን ሲፈጅ ሌሊት በጭለማ
ይረጋገጥ ነበር ቦምብ እንደ ቄጤማ

“መድፉ እያጓራ ታንኩ ሲንተከተክ
ሶላቶው ደንግጦ ሲያምጥ፣ ሲብረከረክ
ማሩኝ! ብሎ መሬት ሲወድቅ፣ ሲማረክ

“ሶላቶው ቢያቅተው መቋቋም ካበሻ
አርበኛን ለማጥፋት በዳዋ፣ በጥሻ
መርዝ ጭሱን ነፋው በኣየር መተኰሻ

“ስንቱ ጐበዝ ጀግና ኣለቀ በከንቱ
ደሙን ኣፈሰሰ፣ ተሰዋ ሕይወቱ
ለእናት ኣገሩና፣ ለልጁ፣ ለሚስቱ

“ከዚያም ወደ ደቡብ ሆለታ መጥተን

መናገሻ ጫካ ከዋሻ ገብተን
አምስቱን ዓመታት ታገልን ሸፍተን

“ሃይሌ ተክላይ ዋዛ አሽከር መስሎ ገብቶ
አስተርጓሚ ነበር ቀን-ቀን ለሶላቶ
ግን አለቃችን ነው ሌሊት-ሌሊት መጥቶ

“እርሱ በሚነግረን ደፈጣ አዘጋጅተን
የጣልያንን ምሽግ ደጋግመን መትተን
ብዙ አስጨነቅናቸው መድረሻ አሳጥተን

“አንድ ቀን ከሩቁ ጥቁር ታንክ ሲመጣ
እኔና ያዕቆብ አድርገን ደፈጣ
ተደብቀን ነበር ከእሾኽ፣ ከጋሬጣ

“አክስትሽ ዓለም-ጣይ ጀግና፣ አርበኛዋ
ጥርሷን ፈገግ አርጋ ያቺ ዘዴኛዋ
ታንኩን አቆመችው፣ ወይ ተንኰለኛዋ!

“ከታንኩ ሊወርድ ሲል በጥይት መታሁት
ሁለተኛውንም ብቅ ብሎ እንዳየሁት
አነጣጠርኩና ደግሜ ቀላሁት

“ግን ይቅር ሊሞቱስ መቸ ወደቁና
ጠመንጃ ለመምዘዝ ሲሉ ጐምበስ-ቀና
አባ ያዕቆብ ደግሞ አንዴ ተኰሰና

“መዝዞ ጐራዴውን አንገት፣ አንገታቸው
ሁለቱን ሶላቶ ደጋግሞ መታቸው
ጭንቅላታቸውን ቆራርጦ ጣላቸው

“ታንኩም ጢቅ ብሎ መሣሪያ ሞልቷል
ለብዙ የሚሆን ሢሳዩ ተከፍቷል
ጠመንጃ፣ ሽጉጡ፣ ቦምቡ ተዘጋጅቷል

“መሣሪያውን ሁሉ አንድ-በአንድ ለቅመነው
መንገደኛውን ሰው ጠርተን አሸከምነው
ታንኩንም ቀፎውን በእሳት አጋየነው

“ከዚያ መሣሪያውን ከዋሻ ደብቀን
ለብዙ አርበኛ ጠርተን አከፋፍለን

ጠላትን መታነው ደግመን፣ ደጋግመን

“ይኸ ሁሉ ሆኖ ወራሪው ሲሸነፍ
ኣገሩ ሲመለስ፣ ኣርበኛው ሲሰለፍ
ባንዴራችን ባዲስ ሓር ላይ ሲጠለፍ

“ጠላት እንዲወጣ የኢትዮጵያ ኣባዜ
ስለት ገብቶ ኖሮ በወረራው ጊዜ
‘ትዳርም ኣልፈልግ፣ ሙሽራና፣ ሚዜ…’

“ዓለም በቃኝ ብሎ ከሴት ላይደርስ እርም
ጀግናው ሃይለ ተክላይ ያለም-ጣይ ወንድም
ኑሮውን ፈጸመው ገብቶ ከገዳም

“ታሪኩ ይኸው ነው ያውልሽ ባጭሩ
ወገን የሚያኰራ ስንት ጀብዱ የሠሩ
ሽማግሌዎችሽ ኣርበኞች ነበሩ

“ኣጐትሽ ያዕቆብም ነብሱን ይማርና
ኣደራ ያለኝ ቃል ስሚኝ በጥሞና
ለወሬ ነጋሪ ዛሬ ኣድገሻልና

“ኣዲስ ዘመን መጥቶ ዘመናትም ቢያልፉ
በጥጋብ ሶላቶች ስንት የተለከፉ
በሓበሻ መሬት መርዝ ያርከፈከፉ

“ከቶ እንዳይረሳው ትውልድ ይታዘበው
ጋዜጣና፣ ራድዮ ደራሲም ይዝገበው
የፈጁትንም ሰው ታሪክ ይመዝግበው

“እንዲያው ለሰው ይምሰል ቢነጣ ቆዳቸው
ከጥቁሩ ሸሚዝ ይጠቁራል ልባቸው
እግዜር በብልሓቱ ኣርቆ ያጥፋቸው

“አዲስ ዘመን መጥቶ አሮጌውም ቢያልፍ
ሰዉ ችላ ብሎ ትቶት እንዳያርፍ
ዓለም እንዳይረሳው የሠሩትን ግፍ

“ሰው ሁሉ ይወቀው፣ ዓለሙ በይፋ
ኣንድ ብለሽ ከስሩ ኦሜጋና ኣልፋ
ደጋግመሽ ንገሪ ታሪክ እንዳይጠፋ።”      ገ/ኢ. ጐርፉ።